# ከክልል የጤና ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት የቁጥጥር ሥራውን ውጤታማ እያደረገው ነው

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣትና አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ በተለያዩ ክልሎች ከከፈታቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መካከል የጅማ ቅርንጫፍ አንደኛው ነው፡፡

ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱም በአምስት ክልሎች ማለትም በኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ በጋምቤላና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡



አቶ በቃሉ አረጋ

የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ በቃሉ አረጋ፣ የ2016 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ዕቅድ አፈፃፀም አስመልክተው መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ በመግለጫቸውም «ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የዕቅዱን 78 በመቶ አከናውኗል፣ ይህም ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ነው» ብለዋል፡፡

እንደ አቶ በቃሉ ገለፃ፣ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከየክልሎቹ ጤናና ጤናነክ ግብዓቶች ጥራት ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በመሆን ስጋት ተኮር የድህረ ፍቃድ የምግብ ደህንነት ቁጥጥር፣ የምግብ ተቋማት የውስጥ ጥራት ሥርዓት እንዲዘረጉ የማድረግ፣ በቀላሉ ለብልሽት ተጋላጭ የሆኑ በ8 የምግብ ምርቶች ላይ ቁጥጥር የማድረግ ውጤታማ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡

የምግብ ችርቻሮ ድርጅቶች (የባልትና ተቋማት፣ የምግብና መጠጥ አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ ሆቴል፤ ሬስቶራንት፣ የቄራ ድርጅቶችና ሉካንዳ ቤቶች፣ ወዘተ) ላይ በየወሩ 10 ቀናት የገበያ ቅኝት እንዲሁም የመንገድ ላይ ምግብ ሻጭ ተቋማት የመልካም ንጽሕና አጠባበቅ (GHP) እና መልካም የአበሳሰል ሥርዓት (GCP) እንዲዘረጉ የማድረግ ተግባራትም አከናውኗል፡፡

የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያን የመቆጣጠር፣ አገልግሎት ላይ የማይውሉ ምግቦችን በአግባቡ መወገዳቸውን ማረጋገጥ እና በተመረጡ የምግብ ዓይነቶች ላይ ለድህረ ገበያ ጥራት ምርመራ ናሙና መሰብሰብ እንዲሁም የተጠረጠሩ (በቁጥጥር ወቅትና በሕዝቡ ጥቆማ) የምግብ ናሙናዎች ላይ የጥራት ምርመራ እንዲሠራ ወደ አዲስ አበባ መላክም ሌሎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ በመንፈቅ አመቱ ካከናወናቸው ዐብይ ተግባራት መካከል ናቸው፡፡

በተለያዩ ቦታዎች በሕገ-ወጥ የምግብ ንግድ፣ ደረጃውን ያልጠበቁ እና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ባለፈባቸው የምግብ ምርቶች ላይ በየወሩ 10 ቀናት የገበያ ቅኝት ማድረግና በሕገ ወጥ የምግብ ንግድ ዝውውርና ቅየጣ ላይ የሰርቬላንስ ሥራ መሥራት እና ኦፕሬሽን የመውሰድ ሥራም በአግባቡ ተከውኗል፡፡

ከቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ በወሰዱ የምግብ አምራች፣ አስመጪ አከፋፋይና ላኪ የምግብ ተቋማት ላይ የጋራ ቁጥጥር የተደረገ ሲሆን፣ በተለይ በአጋሮ ከተማ እና በጋምቤላ ከተማ በሚገኙ የቄራ አገልግሎት ላይ የጋራ ኢንስፔክሽን በማካሄድ በታዩ ክፍተቶች ላይ ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድም ተደርጓል፡፡

እንደ አቶ በቃሉ መግለጫ በበጀት አመቱ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በአጠቃላይ ከዘጠኝ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመቱ የተቀየጠ የማርና የቅቤ ምርትና የመጠቀሚያ ጊዜቸው ያለፈባቸው ብሎም ከደረጃ በታች የሆኑ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ለኅብረተሰቡ ሳይሰራጩ በቁጥጥር ስር በማዋል እንዲወገዱም ተደርጓል፡፡ ቀሪዎቹን የማስወገድ ሂደትም ተጀምሯል፡፡

ደረጃቸውን ያልጠበቁ እና የተጭበረበሩ መድኃኒቶች ስርጭት በማስቆም ረገድ በሕገ-ወጥ የመድኃኒት አዘዋዋሪዎች ላይ በየወሩ 10ቀን የገበያ ላይ ቅኝት በማድረግ በ81 የመድኃኒት ችርቻሮ ድርጅቶች እና በ48 የተለያዩ ደረጃ ባላቸው ክሊኒኮች ላይ በአራት ክልሎች፣ ማለትም በጋምቤላ ክልል፤ በጋምቤላ ከተማ፤ በላሬ፤ በኢታንግ እና በፉኙዶ፤ በኦሮሚያ፤ በጅማ ዞን፤ በአጋ ከተማ፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉአባቦራ ዞን፣ በመቱና በደምቢዶሎ ከተማ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች፤ በቤንች ሸኮ እና በሸካ ዞን በተጨማሪም በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ በሳጃና ፎፋ ከተሞች ከአምስት ጊዜ በላይ ከክልል ተቆጣጣሪዎች ጋር በመሆን የቁጥጥር ሥራ መሥራት ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት ግምታዊ ዋጋቸው ከ3ነጥብ 1 ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ሕገወጥ መድኃኒቶች በቁጥጥር ስር ማዋል ተችሏል፡፡

የመድኃኒትና የክትባት ደህንነት ክትትል ሥራን በማጠናከር በኩል የመድኃኒት የጎንዮሽ ጉዳት እና የክትባትና ከክትባት በኋላ የሚከሰት የጎንዮሽ ጉዳት ክትትል ማድረጊያ ሪፖርቶች ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ የPV ሴንተር እንዲላክ ተደርጓል፡፡

የተለያዩ የሴንሲታይዜሽን፤ የገጽ-ለገጽ ውይይቶችን፣ የማጠናከሪያ ሥልጠናዎች ቅርንጫፉ አገልግሎት በሚሰጥባቸው አካባቢዎች ስር ላሉ የጤና ተቋማት ሠራተኞችና ለሚመለከታቸው አካላትም ተሰጥቷል፡፡

ከUSP/PQM ጋር በመሆን በ47 ጤና ተቋማት ላይ የክትባት የቅዝቃዜ ሰንሰለት Calibration እንዲሠራ ሲደረግ በ60 ጤና ተቋማት የክትባት የቅዝቃዜ ሰንሰለት ያለበት ሁኔታ እንዲታወቅ የዳሰሳና የዳግም ዳሰሳ ሥራ ተከናውኗል፡፡

አቶ በቃሉ እንደሚያስረዱት፣ በተጠቀሰው ወራት ግምታዊ ዋጋቸው ከ1ነጥብ9 ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ሕገወጥ የትምባሆ ምርቶች በቁጥጥር ስር ውለው ተወግደዋል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ስድስት ወራት በምግብና ጤና ግብዓቶች ሕገወጥ ዝውውር ዙሪያ ተሳታፊ በሆኑ 17 ግለሰቦች ላይ ክስ ተመስርቶባቸው ጉዳያቸው በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ከበር መልስ በ10 ሜትር ክልል ማጨስ የተከለከለባቸው 91 የግል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የ(ሆቴል፤ ግሮሰሪ፤ የቡና እና ሻይ ቤቶች፤ ቁርስ ቤቶች) ላይ ቁጥጥር በማድረግ ግንዛቤ የመፍጠር እና ማጨስ ክልክል መሆኑን የሚገልጽ ስቲከር የመለጠፍ ሥራም ተሠርቷል፡፡

ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ጋር በመሆን ቦንጋ ከተማን ከትምባሆ ጪስ ነፃ ለማድረግ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና እና የቁጥጥር ማስጀመሪያ ለ70 ተሳታፊዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

በምግብና ጤና ግብዓቶች ዙሪያ የተከናወነው የቁጥጥር ሥራ ከክልል ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በቅንጅት የተከናወነ ሲሆን የትብብር ሥራውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ መጥቷል፣ ከክልል የጤና ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት የቁጥጥር ሥራውን ውጤታማ እያደረገው ነው፡፡

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482

http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ